# ግጥም በያይነቱ

**በዘውገ ፋንታ**
ነሐሴ 2010

ደሴ ይብቃህ ተነስ፣
እምቢ! አለ አደዋ፣
ጎጃም ቆሎ ድረስ፣
ፍቼ ገብቷል ሸዋ።

ሐማሴን ና ወረድ፣
ተከዜም ቢሞላ፣
በጎንደሩ መንገድ፣
ተሻገር በመቀላ።

ባደሜ ቅበር ዘመዴ፣
አሰብን ጨው በላ፣
ተከዜ ይታገድ፣
ከዚያ ወሃ ይፍላ፣
ከላይ አለ ጉድ፣
ይመጣል በኋላ።

ቤት እንስራ አልጋ፣
አሁን እናመቻች፣
ጠጋ በል ወለጋ፣
ሀረርጌ ገጥሟለች፣
ባሌን ፈልጋ፣
አሩሲን አቅፋለች።

ኢሊባቡር ይምጣ፣
ገመቶፋን ይዞ፣
ሲዳሞ ካልወጣ፣
ምን ይዞ ጉዞ!
ሁሉም የኛ ዕጣ፣
ይድረስ ተያይዞ፣
ተቃቅፎ ይምጣ፣
ወገን ተጋግዞ፣
ቃስወርድ ያወጣ፣
እንግዳን ልጅ መዞ፣
ኢትዮጵያ አትቆጣ፣
በዚች ትንሽ ጣጣ።

በሉ ወሎ መጇን!
አወሉ ደርሶናል፣
በረካ ከጠጣን፣
መንገዱ ይቀናል።

ጥጋብ ነው ርሃብ፣
የበላው ያልቅስ፣
ክተት! በል በደቡብ፣
አይቅር አንድ ነፍስ፣
ይግባ ይመዝገብ፣
የሰሜኑም ይድረስ፣
ያለው በምዕራብ፣
የወጣው ይመለስ።